www.asrc.org.au

**Asylum Seeker Resource Centre**
ABN 64114965815 • Incorporation No: A0042918

12 Batman Street, West Melbourne
Victoria 3003, Australia

t: 03 9326 6066
f: 03 9326 5199

# እንኳን ደህና መጡ

ወደ ጥገኝነት ፈላጊ መገልገያ ማእከል እንኳን ደህና መጡ። በማንም ተጽእኖ የለለብን የሰብአዊ መብቶች አስከባሪ ድርጅት ነን። ለመንግሥት የምንሠራ ድርጅት አይደለንም። የምናቀርበው እርዳታ በነጻ ይሆናል። በአውስትራሊያ ውስጥ ጥገኝነት ለሚፈልጉ ሰዎች ሰብአዊ መብታቸው እንዲከበርና እንዲጠበቅ እንረዳለን። ሰዎች በሞላ ነጻ መሆን እንዳለባቸው እናምናለን።

## ማንን እንደምንረዳ

ጥገኝነት ፈላጊዎችን የምንረዳ ነን። ጥገኝነት ፈላጊ የሚሆን ሰው:

- በሃገራቸው ለመኖር በጣም አደገኛ በመሆኑ ከአገሩ መልቀቅ ያለበት እና
- በሃገራቸው ውስጥ በስጋት ላይ ላሉ ምክንያቱም በሚኖራቸው የጎሳ፣ የፖለቲካ ፍላጎት፣ ሃይማኖት፣ የትውልድ ዘር፣ የብሄር ዜግነት ወይም የማሕበራዊ ቡድን ሳቢያ ከፍተኛ ጉዳት ለደረሰባቸው ወይም በከፍተኛ ችግር ውስጥ ላሉ፣ እና
- ካለባቸው ከፍተኛ ጉዳት መንግሥታቸው ሊከላከልላቸው የማይችል ከሆነ ነው።

## እንዴት ልንረዳዎ እንደምንችል

በአውስትራሊያ ውስጥ እርስዎ ስደተኛ መሆን ቀላል ላለመሆኑ ማረጋገጥ። በስደተኛ መልኩ ተቀባይነት ስለሚኖርዎ እድል ትክክለኛ የሆነ ህጋዊ ምክር በነጻ እናቀርብልዎታለን። ስደተኛ ለመሆን የሚችሉ መስሎ ካሰብን እንረዳዎታለን። ማንም ሰው ጥገኝነት ፈላጊ ለመሆን እንደማይመርጥ እናውቃለን ታዲያ ለዚህ ነው አስቸጋሪ ጊዜ ሲከሰት ባሉበት ቦታ ልንረዳዎ የምንገኘው።
እርስዎን ለመርዳት የተቻለንን ያህል እንጥራለን፤ ይህም በማንኛውም ነገር ማለት ህጋዊ የሆነ ምክር፣ የህክምና እንክብካቤ፣ መድሃኒቶች፣ ለልጅዎ የቅዘን ጨርቅ/ናፒ፣ በየቀኑ ጤናማ የሆኑ ምሳዎች፣ ሥራ ለመፈለግ እንዲሞክሩ ሊረዳ የሚችል በሜልበርን ውስጥ ስለሰፈራ መግለጫ ይቀርባል። የሚነግሩን ማንኛውም ነገር በሚስጢር ይጠበቃል እንዲሁም በማእከላችን ላይ ደህንነትዎ የተጠበቀ ይሆናል።

## እንዴት ሊያገኙን እንደሚችሉ

በሜልበርን ውስጥ የጥገኝነት ፈላጊ ከሆኑ እርዳታ ለማግኘት ከሰኞ እስከ ዓርብ ከጥዋቱ 10am እስከ ሰዓት በኋላ 5pm ባለው ጊዜ በአካል ወደ ማእከላችን መምጣት ይችላሉ። አድራሻችን፡ 12 Batman Street, West Melbourne ይሆናል። እንዲሁም እርዳታ ለማግኘት በስልክ (03) 9326 6066 አድርጎ በተጠቀሱት ሰዓታት ውስጥ ሊደውሉልን ይችላሉ።




**የጥገኝነት ፈላጊ መገልገያ ማእከልን በሚከተሉት ዘዴዎች ማግኘት ይችላሉ:**

እኛ የምንገኘው በKing Street እና Batman Street መታጠፊያ መንገድ ላይ ሲሆን ከከተማ ሲመጡ ከፍላግስታፍ አትክልት ቦታ/Flagstaff Gardens ያለውን መንገድ አቋርጦ ነው።

- በከተማ ውስጥ ከፍላግስታፍ/Flagstaff ወይም ከሳውዘርን ክሮስ/Southern Cross ባቡር ጣቢያ በእግር መጓዝ ሲችሉ ይህም የ5 ደቂቃ ጉዞ ነው።
- በከተማ ዙሪያ የሚጓዝ ትራምን መያዝ ሲችሉ ታዲያ በ La Trobe Street እና King Street መንገድ ጫፍ ላይ መውረድና ከዚያም በእግር የ2 ደቂቃ ጉዞ ይሆናል።

**በአውስትራሊያ ሆነው በሜልበርን ውስጥ ካልሆኑስ ምን ይደረጋል?**

በሜልበርን ውስጥ ላሉ ጥገኝነት ፈላጊዎች ብቻ መርዳት እንችላለን። በሌላ አስተዳደር ግዛት ውስጥ ከሆኑ በአቅራቢያዎ ያለን አገልግሎት ለማግኘት ከዚህ በታች ያለውን ይጫኑ።

http://www.asrc.org.au/media/documents/asrc-resource-directory.pdf

ከአውስትራሊያ ውጭ ከሆኑና በዓለም ዙሪያ ለጥገኝነት እንዴት ማመልከት እንደሚችሉ መረጃ ከዚህ በታች ያለውን ማገናኛ ይጫኑ:

http://www.asylumlaw.org/asylumseeker